የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21[st] Year No 58
ADDIS ABABA 31[st] July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፫/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለአክሱም ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…………………………………………………………ገጽ ፰ሺ፪፻፹

CONTENTS

Proclamation No. 913/2015

Kuwait Fund for Economic Development Loan Agreement For Financing the Axum Water Supply Project Ratification Proclamation …..……..Page 8280

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፫/፪ሺ፯

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአክሱም ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፮ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ የኩዌት ዲናር (ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የኩዌት ዲናር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ ጁን ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No 913/2015

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND KUWAIT FUND FOR ARAB ECONOMIC DEVELOPMENT ASSOCIATION

Whereas, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development stipulating that the Kuwait Fund for Arab Economic Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Six million five hundred thousand Kuwaiti Dinars (K.D 6,500,000) for Axum Water Supply Project, was signed in Addis Ababa on the 16[th] day of June 2015;

Whereas, the House of people's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7[th] day of July/2015;

Now, Therefore, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአክሱም ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፫/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት እ.ኤ.አ ጁን ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 922 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፮ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ የኩዌት ዲናር( ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ የኩዌት ዲናር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as ''Kuwait Fund for Economic Development Loan Agreement for Financing the Axum Water Supply Project Ratification Proclamation No. 913/2015".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement No 922 signed in Addis Ababa between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development on the 16th day of June 2015 is ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Six million five hundred thousand Kuwaiti Dinars (K.D 6,500,000) in accordance with the terms and conditions set-forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazzette.

**Done at Addis Ababa on this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR)**

**PRESEIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIREPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት